dc water is life®

David L. Gadis, Chief Executive Officer

DISTRICT OF COLUMBIA WATER AND SEWER AUTHORITY | 1385 CANAL STREET, SE | WASHINGTON, DC 20003

# የሌድ ውሃ አገልግሎት መስመር ማሳሰቢያ

ውድ የአሁን ነዋሪ፡-


በDC Water መረጃ መሠረት፣ በ[**House Address Ave QD**] ቤትዎን ወይም ሕንጻዎን የሚያገናኘው የውሃ አገልግሎት መስመር [public pm] በመንግሥት በኩል እና [private pm] በግል በኩል አለው። የአገልግሎት መስመርዎ ተቀይሮ እንደነበር የሚያሳይ ማስረጃ ካልዎት እባክዎን ከእርስዎ ጋር ለመስራት እንድንችል መዝገቦቻችንን እንድናዘምን ለ**leadtest@dcwater.com** ኢሜል ያድርጉ።

ይህ ደብዳቤ በሌላ ቋንቋ ከፈለጉ፣ እባክዎን ወደ Lead Free DC በ 202-787-4044 ይደውሉ ወይም የተተረጎሙትን የደብዳቤውን ስሪቶች በመስመር ላይ በ**www.dcwater.com/SL-material-notice** ይመልከቱ ወይም የQR ኮድን በቀኝ በኩል በመቃኘት ይመልከቱ። . እወቅ።

## ሌድ የሚያመጣቸው የጤና መዘዞች

በመጠጥ ውሃ ውስጥ ለሌድ መጋለጥ በሁሉም የዕድሜ ክፍሎች ላይ ከባድ የጤና ችግሮች ያስከትላል። ጨቅላ ሕጻናት እና ልጆች የIQ እና የትኩረት መስጠት መቀነስ ሊያጋጥማቸው ይችላል። ለሌድ መጋለጥ አዲስ የመማር እና የባህርይ ችግርን ያስከትላል ወይም ነባር የመማር እና የባህርይ ችግሮችን ያባብሳል። ከእርግዝና በፊትም ሆነ በእርግዝና ወቅት ለሌድ የተጋለጡ የሴቶች ልጆች ለእነዚህ አሉታዊ የጤና ችግሮች የመጋለጥ ዕድላቸው ይጨምራል። አዋቂዎች ለልብ ሕመም፣ ለከፍተኛ ደም ግፊት፣ ለኩላሊት ወይም ለነርቭ ሥርዓት ችግሮች የመጋለጥ ዕድላቸው ከፍ ሊል ይችላል።

### ስለ ውሃ አግልግሎት ቱቦዎ መረዳት




## የሌድ አገልግሎት መስመሮችን መቀየር

በDC Water ወይም በንብረቱ ባለቤት አነሳሽነት - የDC Water የሌድ አገልግሎት መስመርን ለመቀየር በርካታ ፕሮግራሞችን ያካሂዳል።

### በDC Water አነሳሽነት የሚደረጉ የሌድ ቅያሬዎች - ነጻ ሙሉ የሌድ አገልግሎት መስመር ቅያሬዎች

አነስተኛ ዲያሜትር ያለው ዋና የውሃ መስመር መተካትን፣ ብሎክ በብሎክ የውሃ አገልግሎት መስመር መተካትን እና የዲስትሪክት የትራንስፖርት መምሪያ ፕሮጀክቶችን ጨምሮ የDC Water ከታቀዱ የካፒታል ማሻሻያ ፕሮጀክቶች ጋር በጥምረት እየሠራ የሌድ አገልግሎት መስመሮችን ይቀይራል። የDC Water በተጨማሪም ባልታቀዱ ድንገተኛ የውሃ አገልግሎት መስመር ጥገና ፕሮጀክቶች ወቅት የሌድ አገልግሎት መስመሮችን ይተካል። እነዚህ የአገልግሎት መስመር ቅያሬዎች በነፃ ናቸው።

የDC Water በግል ቤትዎ ላይ ያለውን የውሃ አገልግሎት መስመር እንዲተካ የቤቱ ባለቤት/የተፈቀደለት ሰው (ነዋሪ ወይም ሌላ አካል) የመግቢያ ፍቃድ ሙብት ቅጽን ማንበብ፣ መሙላት፣ መፈረም እና መመለስ አለበት። ፈቃድ ያለው ሰው ባለቤቱን እንዲወክል እንደተፈቀደለት የሚያሳይ ከቤቱ ባለቤት ባለ ማረጋገጫ ደብዳቤ ወይም ሌላ ሕጋዊ ሰነድ ማቅረብ አለበት። ፈቃድ መስጫ ቅጽ የሚገኘው በ **http://www.dcwater.com/ROE**ነው።

አድራሻዎን ለመፈለግ እና ለአካባቢዎ የታቀዱ ፕሮጀክቶች መኖራቸውን እና እነዚያን ፕሮጀክቶች ለማጠናቀቅ የታቀደው የጊዜ ሰሌዳ ምን እንደሚመስል ለማየት የግንባታ ዳሽቦርዳችንን ይጎብኙ። የግንባታ ዳሽቦርዱ የሚገኘው በ:-**www.dcwater.com/lead-construction-dashboard** ነው።

### በደንበኛ አነሳሽነት በግል በኩል ብቻ* የሌድ ውሃ አገልግሎት መስመር ቅያሬዎች - በDOEE በኩል ነጻ ነው

በግል ቤቱ ላይ የሌድ ውሃ አገልግሎት መስመር እና በሕዝብ ቦታ ላይ የሌድ ያልሆነ የውሃ አገልግሎት መስመር ላላቸው፣ የDistrict's Lead Pipe Replacement Assistance Program (LPRAP) (የዲስትሪክቱ የሌድ ቧንቧ መቀየሪያ እርዳታ ፕሮግራም) ለቅያሬው ለመክፈል የሁለቱንም የዲስትሪክት እና የDC Water የBipartisan Infrastructure Law (BIL) (የሁለትዮሽ መሠረተ ልማት ህግ) ገንዘቦችን ይጠቀማል።

የቤት ባለቤቶች በ**www.doee.dc.gov/service/lead-pipe-replacement-assistance-program** የሚገኘውን የDistrict Department of Energy and Environment (DOEE) (የዲስትሪክት ኤነርጂና አካባቢ መምሪያ) ማመልከቻ መሙላት አለባቸው።

### በደንበኛ ተነሳሽነት ሙሉ የሌድ አገልግሎት መስመር ቅያሬዎች

ሁለቱም የህዝብ እና የግል የውሃ አገልግሎት መስመሩ ክፍሎች የሌድ ከሆኑ እና ለአካባቢው የካፒታል ማሻሻያ ፕሮጀክቶች ካልታቀዱ፣ ደንበኞች በVoluntary Full Replacement Program (በፈቃደኝነት ሙሉ መቀየሪያ ፕሮግራም) ውስጥ መመዝገብ ይችላሉ። የንብረቱ ባለቤት በገዛ ፍቃዱ በግል ንብረቱ ላይ ያለውን የሌድ ውሃ አገልግሎት መስመር ክፍል በራሱ ወጪ ለመተካት ከወሰነ፣ DC Water በሕዝብ ቦታ ያለውን የሌድ ውሃ አገልግሎት መስመር ክፍል ይቀይራል። በDC Water አነሳሽነት የግንባታ ፕሮጀክቶች ወቅት ከመቀየር ጋር በሚመሳሰል መልኩ፣ DC Water በሕዝባዊ ቦታ ለሚሠሩ ሥራዎች በሙሉ ክፍያ ይከፍላል እንዲሁም ሁለቱም ክፍሎች በተመሳሳይ ጊዜ እንዲቀየሩ ሥራውን ያስተባብራል። የንብረቱ ባለቤት ለግል ንብረት ሥራው ይከፍላል።

የትኛው መቀየሪያ ፕሮግራም ለቤትዎ ተስማሚ እንደሆነ ለመነጋገር**www.dcwater.com/lead**ን ይጎብኙ፣ በ**lead@dcwater.com** ኢሜል ያድርጉ፣ ወይም በ202-787-4044 ይደውሉ።

ልብ ይበሉ፦ የአገልግሎት መስመር የመቀየር ሥራ ሌድ ከቤት ውስጥ የውሃ ቧንቧዎች ወደ ውኃ ውስጥ ሌድ እንዲገባ ሊያደርግ ይችላል። DC Water ከግንባታው በኋላ ለሌድ ተጋላጭነትን ለመቀነስ የውሃ ማጣሪያ እና መመሪያዎችን ይሰጣል።

## በመጠጥ ውሃ ውስጥ ለሌድ ተጋላጭነትን ለመቀነስ ሊወስዷቸው የሚችሏቸው እርምጃዎች

እርስዎ ወይም ቤተሰብዎ በመጠጥ ውሃ ውስጥ ለሌድ ያላቸውን ተጋላጭነት ለመቀነስ በተናጥል ወይም በጥምረት ሊወስዷቸው የሚችሏቸው የሚመከሩ እርምጃዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል። ዝርዝሩ ተጨማሪ መረጃ የሚያገኙበትን ቦታ ያካትታል ሆኖም የተሟላ ዝርዝር እንዲሆን ታስቦ ሳይሆን ወይም ሁሉም እርምጃዎች በመጠጥ ውሃ ውስጥ ያለውን ሌድ እኩል ይቀንሳሉ ለማለት ታስቦ አይደለም።

- **ከመጠጣትዎ እና ምግብ ከማብሰልዎ በፊት ውሃዎን ያጣሩ**

ሌድ ያለው ቧንቧ  ውሃዎን ሊበክል ይችላል እንዲሁም የሌድ አገልግሎት መስመሮች የሌላቸው አሮጌ ሕንፃዎች እና በአንዳንድ አዳዲስ ሕንፃዎች ውስጥም ጨምሮ በሁሉም ህንፃዎች ይገኛል ማለት ይቻላል። እራስዎን እና ቤተሰብዎን በውሃዎ ውስጥ ካለው ሌድ ለመጠበቅ ከፈለጉ፥ የሚጠቀሙበት ቦታ ላይ የሚገጠሙ (POU) የውሃ ማጣሪያዎችን በመደበኛነት እንዲጠቀሙ እንመክራለን። እነዚህ ማጣሪያዎች የወጥ ቤት ቧንቧ ላይ ወይም የመጠጥ ወይም የማብሰያ ውሃ ከሚቀዱበት ቦታ ላይ ይገጠማሉ። የPOU ማጣሪያዎች በቧንቧ ላይ የተገጠሙ፣ በጆግ መልክ፥ ከጠረጴዛ ላይ ቁጭ የሚሉ፣ የፍሪጅ እና የውሃ ጠርሙስ ማጣሪያዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ሌድን ለማስወገድ በ***NSF/ANSI 42 ስታንዳርድ*** ለክፍል I ቅንጣት ቅነሳ እና ለሚሟሟ እና ብናኝ ሌድ ቅነሳ በ***NSF/ANSI 53 ስታንዳርድ*** መረጋገጥ አለባቸው። ***የNSF/ANSI 53 ስታንዳርድ ማረጋገጫ ማጣሪያው ሌድን ለመቀነስ የተረጋገጠ መሆኑን መግለጽ አለበት።*** ማጣሪያው ውጤታማ እንዲሆን አጠቃቀሙ በአግባቡ መሆን አለበት። መለወጫውን እንዴት በትክክል መጫን፣ ማቆየት እና መተካት እንደሚችሉ ለማወቅ ከማጣሪያው ጋር የሚመጡትን መመሪያዎች ያንብቡ። መለወጫው ጊዜው ካለፈ በኋላ መጠቀም ሌድን ለማስወገድ ውጤታማነቱን እንዲቀንስ ያደርገዋል። በማጣሪያው ውስጥ ሙቅ ውሃ አያፍስሱ። የቤት ውሃ ማጣሪያዎች ሲስተሞችን በተመለከተ ለበለጠ መረጃና ምክር፣ የEPAን ድረ ገጽ ይጎብኙ በ **www.epa.gov/water-research/consumer-tool-identifying-point-use-and-pitcher-filters-certified-reduce-lead**።

- **አየር ማናፈሻዎን ያጽዱ**

የቧንቧዎን ስክሪን (እንዲሁም አየር ማናፈሻ በመባል ይታወቃል) በየጊዜው ይንቀሉና ያጽዱ። ደለል፣ ፍርስራሾች እና የሌድ ቅንጣቶች በአየር ማናፈሻዎ ውስጥ ሊከማቹ ይችላሉ። የሌድ ቅንጣቶች አየር ማናፈሻው ውስጥ ከተሰኩ፣ ሌድ ወደ ውሃዎ ውስጥ ሊገባ ይችላል።

- ***ቀዝቃዛ ውሃ ይጠቀሙ***

ሌድ ሙቅ ውሃ ውስጥ በቀላሉ ስለሚቀልጥ ለመጠጣት፣ ምግብ ለማብሰል ወይም የሕፃን ፎርሙላ ለማዘጋጀት ከቧንቧ ሙቅ ውሃ አይጠቀሙ ። ውሃውን ማፍላት ሌዱን ከውሃው አያስወግደውም።

- ***ከመጠጣትዎ ወይም ምግብ ከማብሰልዎ በፊት ቀዝቃዛ ውሃውን ትንሽ ያፍስሱት***

ውሃ በቱቦዎቹ ውስጥ በቆየ ቁጥር፣ ይበልጥ ሌድ ሊይዝ ይችላል። ከመጠጣትዎ በፊት፣ የሽንት ቤት ውሃውን በመልቀቅ፣ ገላዎን በመታጠብ እና ቀዝቃዛውን ውሃ ከወጥ ቤት ቧንቧ በማፍሰስ የቤትዎ ቧንቧዎች ታጥበው እንዲወጡ ያድርጉ። DC Water የሙቀት ለውጥ እስኪሰማዎት ድረስ እና ለተጨማሪ ሁለት ደቂቃዎች ቀዝቃዛ ውሃውን ማፍሰስ ይመክራል።

- ***ለውሃዎ የሌድ ምርመራ ያስደርጉ***

ነፃ የሌድ መመርመሪያ ዕቃ ለማግኘት እና በሚጠጡት ውሃ ውስጥ ስላለው የሌድ መጠን የበለጠ ለማወቅ ወደ **leadtest@dcwater.com** ኢሜል ይላኩ ወይም የውሃ ጥራት ክፍላችን ጋር በ 202-612-3440 ይደውሉ። የሌድ ምርመራው ናሙናዎች በሚወሰዱበት ጊዜ ያሉትን የሌድ ደረጃዎች የሚያሳይ ቅጽበታዊ እይታ መሆኑን እና የሌዱ ምንጭ ከናሙና ቧንቧው እስከ አገልግሎት መስመር ድረስ ሊኖር እንዲሚችል እንደሚያመለክት ልብ ይበሉ። የአገልግሎት መስመሮችን እና የቤት ውስጥ ቧንቧዎችን የሚያካትቱ የሌድ ምንጮችን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎ **www.epa.gov/ground-water-and-drinking-water/basic-information-about-lead-drinking-water#getinto**ን ይጎብኙ።

## በደሙ ውስጥ ያለውን የሌድ መጠን ለማወቅ ልጅዎን ያስመርምሩ

ቀላል የደም ምርመራ ልጅዎ ለሌድ መጋለጡን ማወቂያ ብቸኛው መንገድ ነው። እባክዎ ዶክተርዎ ሁሉንም ህጻናት ልጆች ቢያንስ ሁለት ጊዜ የሌድ ምርመራ ማድረግ እንዳለባቸው የሚጠይቀውን የዲስትሪክቱን ሕግ የሚከተል/የምትከተል መሆኑን/ኗን ያረጋግጡ። ለልጅዎ ከ6 እስከ 14 ወራት ባለው ጊዜ እና በድጋሚ በ22 እና 26 ወራት መካከል የሌድ ምርመራ እንዲደረግለት/ላት ዶክተርዎን ይጠይቁ። በቀላሉ ማስታወሻ መንገድ:- ሁሉንም ልጅ በtwice-by-two (ከሁለት በፊት ሁለቴ) ማስመርመር:- **www.doee.dc.gov/es/service/every-child-twice-two** ። Centers for Disease Control and Prevention (የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማዕከል) በልጆች ደም ውስጥ ያለው የሌድ መጠን 3.5 ማይክሮግራም በዴሲሊትር (μg/dL) ወይም ከዚያ በላይ በሚሆንበት ጊዜ የሕዝብ ጤና መምሪያ እርምጃዎችን ይመክራል። በተጨማሪም CDC ስለ ደም ምርመራ እና ለሌድ ተጋላጭነትን ስለመቀንስ **www.cdc.gov/lead-prevention/hcp/clinical-guidance/index.html** ላይ መረጃ ይሰጣል።

የዲስትሪክቱ ጤና ጥበቃ መምሪያ (DC Health) ለልጆች የደም ሌድ ምርመራ እና የሌድ መመረዝን መከላከል በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ይሰጣል። ለይበልጥ መረጃ የDC Health's Environmental Health Administrationን (የዲሲ ጤና አካባቢ ጤና አስተዳደር) በ202-442-5955 ያነጋግሩ ወይም **www.dchealth.dc.gov**ን ይጎብኙ።

በመጠጥ ውሃዎ ላይ የሌድ ተጋላጭነትን ለመቀነስ እና የሌድን የጤና ችግሮች በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የEPAን ድረ ገጽ በ**www.epa.gov/lead** ይጎብኙ።

የሌድ የውሃ ቱቦዎችን ለመቀየር እና በአካባቢዎ ያለውን የውሃ አገልግሎት እና ጥራት ለማሻሻል ከደንበኞቻችን እና አጋሮቻችን ጋር አብረን ስንሠራ ለቀጣይ ትብብርዎ እናመሰግናለን።

ከአክብሮት ጋር:-

